የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# የብር ዓይነቶች በአካላቸው ላይ የሚገኙ የደህንነት መጠበቂያ ምልክቶች እና ምስሎች

1. **ተከታታይ ቁጥሮች** — የገንዘቡ ቁጥሮች በሚያጎላ ማሽን ሲታዩ ከጥቁር ወደ አረንጓዴ ፍሎረሰንት ቀለም ይለወጣሉ።

2. **ማየት ለተሳናቸው እውቅና ምልክት** — የብሩን ዋጋ የሚገልጽ ማየት የተሳናቸው በእጅ ዳሰሳ ማወቅ የሚችሉበት የደህንነት መጠበቂያ ምልክት።

3. **ጎርባጣ መስመሮች (PEAK®)** — የባንክ ኖቱ ሲደሰስ የመጎርበጥ ስሜት እንዲሁም የኖቱ ዋጋ ይታያል።

4. **ደማቅ አንጸባራቂ ምልክት** — ገንዘቡ ወደ ላይ ወይም ወደታች ሲዞር የሚንቀሳቀስ ደማቅ የቀለም ፍንጣቂ (SPARK®) የደህንነት መጠበቂያ ምልክት።

5. **የደህንነት መጠበቂያ ክር** — የሚሽከረከር ደማቅ ቀለም ኮከብ አዲስ የደህንነት መጠበቂያ ክር። በክሩ ውስጥ NBE፣ ኢ.ብ.ባ እና የገንዘቦቹ ዓይነት ተጽፎ ይገኛል።

6. **የውሃ ምልክት** — ገንዘቡ ወደ ብርሃን አቅጣጫ ተደርጎ ሲታይ በላዩ ላይ ከሚገኘው ምስል ፊትለፊት ተመሳሳይ ደብዛዛ የውሃ መልክ ያለው ምልክት ይታያል።

7. **ትይዩ ምልክት** — የብር ኖቶች ከብርሃን አቅጣጫ ሲታዩ ኳስ መሳይ ምልክት ከገንዘቡ በስተኋላው ካለው ተመሳሳይ ምልክት ጋር በፍጹም ትይዩ ሆነው በአንድ ቦታ ላይ ያርፋሉ።

8. **ፈሎረሰንስ ምልክት** — አንበሳው ምስል ራስ ላይ አልትራቫዮሌት ጨረር ሲበራበት ወደ ብጫነት የሚለወጥ ፍሎረሰንት ምልክት።



10 ብር - የፊት ገጽታ



10 ብር - የኋላ ገጽታ



50 ብር - የፊት ገጽታ



50 ብር - የኋላ ገጽታ




100 ብር - የፊት ገጽታ



100 ብር - የኋላ ገጽታ



200 ብር - የፊት ገጽታ



200 ብር - የኋላ ገጽታ

## ያስተውሉ!!!

የብር ዓይነቶች በአካላቸው ላይ የሚገኙ የደህንነት መጠበቂያ ምልክቶች ያሉባቸው ናቸው። እነዚህን ያላሟሉ ወይም ተመሳስለው የተዘጋጁ ገንዘቦችን የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ግለሰቦች ካጋጠሙዎት ወዲያውኑ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ / የፀጥታ አካል ያሳውቁ።